# BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## Do you have any hobbies?

## መዝናኛዎች እና የትርፍ ጊዜ እንቅስቃሴዎች

*This is not a word-for-word transcript*

**ምህረተስላሴ**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያን ወደምናቀርብበት Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ምህረተስላሴ እባላለሁ። በዚህ ክፍል የትርፍ ጊዜ መዝናኛን እንዴት መጠየቅ እንደሚቻል ይማራሉ።

ሁለት ሰዎች ስለትርፍ ጊዜ መዝናኛቸው ሲያወሩ እንስማ።

***Helen***
*Do you have any hobbies?*

***Jim***
*Yes, I like watching movies. How about you?*

***Helen***
*I like reading books.*

**ምህረተስላሴ**
ንግግሩን ካልተረዱት ብዙም አይጨነቁ። ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
መጀመሪያ ሄለን ጂምን በትርፍ ጊዜ የሚዝናናበት ልዩ ጊዜ ማሳለፊያውን ‘Do you have…?’ ከአለህ ወይ ከ‘any hobbies’ ጋር አጣምራ ጠይቃዋለች። አንድ ሰው የሆነ ነገር እንዳለው ወይም እንደሌለው ስንጠይቅ ‘do you have’ን እናስቀድምና ‘any’ን በማስከተል መጠየቅ የፈለግነውን እናቀርባለን። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*Do you have any hobbies?*

**ምህረተስላሴ**
ከዚያ ጂም ‘Yes, I like watching movies’ ብሎ መለሰ። አንድን ነገር ማድረግ የሚያስደስትዎ ከሆነ ‘I like’ን ያስቀድሙና በ‘-ing’ የሚጨርስ ቃል ያስከትላሉ። ስለዚህም ምግብ ማብሰል ደስ የሚልዎት ከሆነ ‘I like cooking’ ይላሉ። መጨፈር ደስታ የሚሰጥዎ ከሆነ ደግሞ ‘I like dancing’ ይላሉ።

*Yes, I like watching movies.*

*How about you?*

**ምህረተስላሴ**
ሄለን ከዚያ ‘reading books’ መጻሕፍትን ማንበብ እወዳለሁ ብላለች።
መጻሕፍት ማንበብ እወዳለሁን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*I like reading books.*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ሰዎች ስለሚወዷቸው የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያዎች በማዳመጥ እርስዎ ያሉትን ይገምግሙ።

*Do you have any hobbies?*

*Yes, I like visiting museums. How about you?*

*I like going shopping.*

*Do you have any hobbies?*

*I like horse-riding. How about you?*

*I like drawing pictures.*

**ምህረተስላሴ**
እሺ፤ እስኪ ይሄን ደግመን እንሞክረው። የእንግሊዝኛውን አረፍተ ነገር ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያዳምጧቸዋል።

*Do you have any hobbies?*
*Do you have any hobbies?*

*Yes, I like watching movies.*
*Yes, I like watching movies.*

*How about you?*
*How about you?*

*I like reading books.*
*I like reading books.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱ እንመልከት። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ አለህ?*
*Do you have any hobbies?*

*አዎ። ፊልም ማየት እወዳለሁ። አንቺስ?*
*Yes, I like watching movies. How about you?*

*መጻሕፍትን ማንበብ እወዳለሁ*
*I like reading books.*

**ምህረተስላሴ**
እጅግ ግሩም፤ አሁን ሰዎች ስለሚወዱት የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ መጠየቅ አውቀዋል። ለሄለን ምላሽ በመስጠት ልምምድ ያድርጉ። 'How about you?' በማለት ተከታይ ጥያቄ ማቅረብን አይርሱ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*Do you have any hobbies?*

*I like reading books.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን አጠቃላይ ውይይቱን አንዴ ያዳምጡና መልስዎን ያመሳክሩ።

***Helen***
*Do you have any hobbies?*

***Jim***
*Yes, I like watching movies. How about you?*

***Helen***
*I like reading books.*

**ምህረተስላሴ**
ግሩም፤ አሁን ስለሰዎች የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ እንቅስቃሴዎች በእንግሊዝኛ መጠየቅ ችለዋል። ጓደኛ ይፈልጉና ስለትርፍ ጊዜ ማሳለፊያዎቹ/ዎቿ በእንግሊዝኛ በመጠየቅ ይለማመዱ። ለተጨማሪ የኢሴንሻል ኢንግሊሽ መሰናዶ በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018